**PLATFORM OF ETHIOPIAN PROFESSIONALS' SOLIDARITY FOR SUSTAINABLE DEVELOPMENT**

(PEPSOD – KENYA)

ሰኔ 18 ቀን 2010 ዓ.ም.

ለክቡር አቶ ፍጹም አረጋ
የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፦ <u>በናይሮቢ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ለአገራችን ለማበርከት ስላቀድነው ድጋፍና ትብብር</u>

ሚያዝያ 28 እና 29 ቀን 2010 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ በናይሮቢ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት፣ በዚህ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በእርሳቸው መሪነት በአገራችን እየተካሄደ ያለውን ፈጣን የለውጥ ሂደት የምንደግፍ መሆናችንን መግለፃችንና፣ በምላሹም፣ ግንቦት 2 ቀን 2010 ዓም በቁጥር መ30 – 835/3 በተፃፈ ደብዳቤ በሙያችንና በሌላም አቅማችን በሚፈቅደው ሁሉ አገራችንን እንድንረዳ ጥሪ ያስተላለፉልን መሆኑ ይታወሳል። በዚሁም መሰረት፣ አገራችንን ለመርዳትና ለለውጡ ሂደት አስተዋፅኦ ለማድረግ የገባነውን ቃል ወደ ተግባር ለመተርጎም እንድንችል "በኬንያ የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች መድረክ" ወይም "Platform of Ethiopian Professionals' Solidarity for Sustainable Development" (PEPSoD – Kenya) የተሰኘና የተለያዩ ባለሙያዎችን ያሰባሰበ መድረክ በመፍጠርና የመድረኩንም ሥራ የሚያስተባብሩ አባላትን በመሰየም እንቅስቃሴ ጀምረናል።

በመሆኑም፣ በመድረኩ አባላት የሙያ ስብጥርና በአፋጣኝ አስተዋጽኦ የማድረግ ዝግጁነት ላይ በመመስረት፣ ከዚህ ጋር በአባሪነት በተመለከቱት ዘርፎች ላይ የሙያ ድጋፍ ለማድረግ ተዘጋጅተናል። ለዚህም ተግባራዊነት በክቡርነትዎ በኩል የሚከተሉት ሁኔታዎች እንዲመቻቹልን በአክብሮት እንጠይቃለን።

1. አቅማችንን የበለጠ ለማሰባበብና የተሻለ ውጤታማ ለመሆን እንዲቻል፣ ከተዘረዘሩት ዘርፎች መካከል በመንግስት በኩል የተለየና አጣዳፊ ትኩረት የሚፈልጉ ካሉ እንዲገለጽልን፣

2. ትብብር በምናደርግባቸው የሙያ ዘርፎች ከየትኛዎቹ የመንግስት አካላት ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደምንችልና የጊዜ ብክነትንና የሥራ መጓተትን ለመቀነስ እንዲቻል በእነዚህ አካላት ውስጥ በጉዳዩ ላይ ኃላፊነት ወስዶ ከእኛ ጋር የሚሰራ የስራ ክፍልና ኃላፊ እንዲገለጽልን፣

ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ መልስ እየጠበቅን እንቅስቃሴአችንን የምንቀጥል ሲሆን፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ አቅም በፈቀደ ሁሉ አገራችንን ለመርዳትና የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ ለመደገፍ በቁርጠኝነት መዘጋጀታችንን በድጋሚ እናረጋግጣለን።

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ገዛኸኝ ከበደ

በኬንያ የኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች መድረክ

አስተባባሪ ቡድን ሰብሳቢ

ግልባጭ፤ ለኢፌዲሪ ኤምባሲ፣ ናይሮቢ

አባሪ፤ ትብብር የሚደረግባቸው የሙያ መስኮች